# የታሪክ ትሩፋት

ከሕግ በላይ ራሳቸውን በማድረግ የሚያንዣብቡ አውሬ መሰል መሪዎች በየታሪክ አጋጣሚው እየተከሰቱ ሀገራችን ፍዳዋን ሲያሳይዋት ኖረዋል። በየዘመናቱ ሥልጣን ላይ የወጡ መሪዎች የሚያመሳስላቸው አንዱ አስከፊ ገጽታቸውም ይኸው ባህሪያቸው ነው።  ህጎችን ሲደነግጉ ሳይሆን ሲጥሱ የበለጠ ደስታ ይሰማቸዋል። ለዚህም ነው እራሳቸው ያወጧቸውን ሕጎች እራሳቸው ሲጥሷቸው በገሀድ የሚታየው።

ምንጊዜም ቢሆን የአምባገነኖች ልብ እንደ እሳተ ገሞራ ነው። በእጃቸውም ላይ የሰላም ዘምባባ በፍጹም ማብቀል አይችሉም። በስልጣን ለመቆትና ለመኖር ሲሉ የንጹሃንን ህይወት ያለ አግባብ ይቀጥፋሉ። ያ ደግሞ ከሰው ልጆች ክቡር ህይወት ይልቅ መግደል ቀዳሚው ምርጫቸው መሆኑን በግልጽ ያሳየናል። በእኛ ደም ክብርን፣ በእናቶቻችን እንባ ሙገሳን ለማግኘት የሚቋምጡ፣ ወንድምና እህትን መግደል ክብር የሆነባቸው የቃኤል ቤተመቅደስ አምላኪዎች ዛሬም እንደወትሮው በሀገር ላይ እኩይ ደባ እየሰሩ በክብር ዙፋን ላይ ተቀምጠዋል።

የሰው ህይወት ያጠፋ ሰው ነፍስ ገዳይ ተብሎ ይፈረጃል። በስልጣን ላይ ያሉ መሪዎች ግን በየዘመናቱ፣ የአያሌ የንጹህ ዜጎችን ህይወት በየአደባባዩ እንደጎመን ሲቀጥፉ አብዮታዊ፣ አለያም ህጋዊ እርምጃ ነው ይሉናል። አንድ ሰው የራሱ ያልሆነ ንብረት ያለባለቤቱ ፍቃድ ቢነካ ሌባ መባሉ አይቀርም። ነገር ግን ጨካኝ የሀገር መሪዎች የከበረውን የሰው ሕይወትና የአገር ንብረት በጠራራ ጸሐይ በአደባባይ ሲዘርፉ ጀብዱ እንደሰራ ይከበራሉ። በአንጻሩ የስርዓቱ ሰለባ የሆኑ ዜጎች ግን ለእስራት፣ ለስደት፣ ለሴተኛ አዳሪነትና ለተለያዩ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተግባሮቶች ሲዳረጉ አደገኛ ቦዘኔ፣ አውደልዳይ፣ ኪራይ ሰብሳቢዎች ወ.ዘ.ተ የሚባሉ የውንጀላ ታርጋ ይለጠፉባቸዋል። እነሱና ጋሻ ጃግሬዎቻቸው ግን የሚሠሩት ወንጀል እንደ ሀገር ልማት ተቆጠሮ፣ ጨዋዎችና የለውጥ አርበኞች እየተባሉ ባደባባይ ይሸለማሉ፣ ይዘከራሉ።

ከዚህ አስከፊ የጭቆና አገዛዝ ለመላቀቅ፣ በየዘመናቱ ዜጎች የፍትህ ጥያቄ ማንሳታቸው አልቀረም።  ነገር ግን ጥያቄዎቻቸው በወንጀለኝነት እየተፈረጁ፣ እነሱም የአምባገነኖች የጥቃት ሰለባ ሲሆኑ ኖረዋል። ይኖራሉም። አምባገነኖች ግን የአፈና መረባቸውን ዘርግተው፣ በማናለብኝነት ሀገርን እያጠፉ፣ ታሪክ ይቅር የማይለው ወንጀል በዜጎች ላይ ያለ ርህራሔ እየፈጸሙ፣ በሀገር ፍትህ እያሰፈንን ነው በሚል የሀሰት ነጋሪት ይጎስሙልናል። ምግባረ ብልሹነትንም እያስፋፉ፣ የሀገር ሐብት እየመዘበሩና እያስመዘበሩ፣ የተሻለ ስርዓት በመገንባት ላይ እንገኛለን ይሉናል። እንዲህ አይነቱ ሽፍጥ የፖለቲካ ውንብድና ካልሆነ በስተቀር ከቶ ሌላ ምን ሊባል ይቻላል?

ደግሞስ የዜጎችን ደም ያለ አግባብ አንዲያፈሱ፣ ሐብቷን እንዲመዘብሩ፣ ሉዓላዊነቷንና አንድነቷን እንዲገሱ፣ ሰብአዊ መብት እንዲጥሱ፣ በአፈሙዝ አስገድደው እነዲገዙ ማንስ መብት ሰጣቸውና ነው። ያም ሆነ ይህ አላማቸው ግን አንድና አንድ ነው። እሱም ሕዝቡን በተለያየ መንገድ በመከፋፈል፣ ለመብቱ እንዳይቆም አቅም በማሳጣት፣ የግፍ አገዛዛ ቀንበራቸው ያለርህራሄ እንዲቀጥል ማድረግ ነው።

እውነት ሁልጊዜ መታወቅ፣ አልፎ አልፎም መነገር ይገባዋል። በሀገራችን በሰፈነው አስፈሪ ስርዓትና በአስፈጻሚ ሃይላት ጭካኔ የተነሳ፣ ፍትህ የህይወት ሚስጥር እየሆነ ትውልዱ በምኞት ልጆች እየተሞላ፣ የመንፈስ ፍርፋሪ ተመጽዋች መሆን ከጀመረ ውሎ አድሯል። ዛሬ በተለይም በወያኔ አስተዳደር ወጣቱ ስለሀገር እድገትና ልማት የሚያስብበትንና የሚሠራበትን አፍላ ጉልበት፣ እውቀት፣ ሐብትና ጊዜ በከንቱ እየባከነ ይገኛል። የሀገር እድገት የህልም እንጀራ፣ የዜጎች መብት ደግሞ፣ የዘመን ወርተራ  ሆኗል። ይህንን ታሪክ ይቅር የማይለው የሀገር ጥፋት፣ ለመመከት እንደ አምናና ሐቻምና ሁሉ፣ በአንድ መንፈስ ልንረባረብበት የሚገባ ወቅታዊ ተግባር ነው።

ቀደም ሲል የሀገራችን ወጣቶች የአምባገንን ስርዓትና መሪዎቹን ለመገርሰስ በየዘመናቱ አምረው ሲታገሉ መቆየታቸው የሚታወቅ ነው። የሀገር አንድነትና የዜጎችን መብት ለማስከበር የተጀመረው ይህ የወጣቶች ተጋድሎ በየታሪክ አጋጣሚው አንደውቅያኖስ ድንገተኛ ደራሽ ውሀ በማእበል እየተመታ፣ እየወደቀና እየተነሳ ትውልድ የሚያስቆጥር አሰልችና አዝጋሚ ጉዞ ተጉዞ፣ እነሆ አሁን ያለንበት ደረጃ ደርሷል። በአፍላ እድሜ የተጀመረው ይህ ረዥምና ውስብስብ፣ እልህ አስጨራሽ የመሰዋዕትነት መራራ፣ የትግል ጉዞ፣ ዛሬ ላይ ሆነን በትውስታ ምናብ ስንቃኘው፣ በወቅቱ የነበረው የትግል ቁርጠኝነትና የወኔው ግለት፣ በብዙዎቻችን ዘንድ እንደ ዋሽንት ዜማ አጥንታችንንና ጅማታችንን ሰርስሮ የዘለቀ፣ ከልብ ውስጥ በደም የታተመ ህያው አሻራ ሆኖ ዛሬም ድረስ ይሰማናል።

ባህር ሁሉንም ጅረቶች ወደ ከርሱ እያስገባ ያለርህራሄ እነደሚውጥ ሁሉ፣ ሀገራችንም በህይወቷ ጉያ ውስጥ ተወልደው በተስፋ መንፈስ ሲራመዱ የነበሩ ብርቅዬ ልጆቿ፣ የማህበረሰብን ህጎች አናግታችሁዋል ተብለው በጨካኞችና አምባ ገነኖች ሲዋጡ መስማትና ማየት በእጅጉ ስንጠግብ ኖረናል።

በዚህም ትንቅንቅ ያ ተውልድ ብዙ መሰዋዕትነት እንደከፈለ ማንም አይዘነጋውም።  እንደ እንቦሳ ሮጠው ያልጠገቡ፣ ተናግረው የልነተቡ፣ እንኳን ሞታቸው እንቅልፋቸው የሚያሳሳ፣ ለእኛም ሆነ ለሀገር መኩሪያ የሚሆኑ ጓዶቻችንን፣ ወንድሞቻችንንና እህቶቻችንን፣ በግፍ ከጎናችን የተነጠቅንባቸው፣ የወንድ ምጥ በቁም አምጠን፣ ወኔያችን በውስጣችን ያፈሰስንባቸው እነዛን የጽልመት፣ ቀናቶችና ዓመታት አንኳን እኛ ጠላቶቻችንም ከቶ ሊዘነጓቸው አይችሉም።

ፍትህን በሀገር ለማስፈን የተጀመረው ይህ ህዝባዊ ትግል፣ ሁሉም ዜጋ፣ በተለይም ምሁሩና ወጣቱ በመሪ ድርጅቱ ኢ.ሕ.አ.ፓ ጥላስር ተሰባስቦ ለሀገሩና ለወገኑ ሲል ከአምባ ገነኖች ጋር ጉረሮ ለጉረሮ ተናንቆ በመስዋእትነት የተዋደቀበት ሀዋርያዊ የተጋድሎ መዘክር ነው። ትግል አንቀሳቃሽ ሞተር የሚያገኘው አታጋይ ድርጅት ሲኖር እንደመሆኑ መጠን፣ የኢ.ሕ.አ.ፓን ስምና ህልውና ከመቃብር በላይ ጠብቆ የማቆየት ሐላፊነት ብቻ ሳይሆን ታሪካዊ ግዴታችንም ጭምር ነበር።

ዛሬ ላይ ቆመን፣ የትላንትናውን የትግል ጥሪ ደግመን ማስተጋባት መቻላችን ብቻ በራሱ፣ ትግሉን በግንባር ቀደምትነት ሲመራ የነበረውን፣ የኢ.ሕ.አ.ፓን የትግል ቁርጠኝነትና የአላማ የጽናት ምህዳር፣ ታላቅነት የሚያሳይ ህያው ማስረጃ ነው።

ስለዚህም ትግላችን የፍትህና የነጻነት ተጋድሎ አስኳል የነበረ፣ ብዙዎችን የውጤቱ ምጻተኞች ያደረገ፣ ነፍስና ስጋችንን በቁጭት ሲያሟግት የኖረ፣ በዚህም ይሁን በመጪው ትውልድ ዘንድ ሲታሰብ የሚኖር፣ የቁርጥ ቀን ልጆች የተጋድሎ ታሪክ ነው።

በየዓመታቱ ጣልቃ ያጋጠሙትን ፈተናዎች በጽናት አሻገሮ፣ እነሆ ከሁላችን ጋር በመንፈስ ሳይደበዝዝ የኖረ፣ በሀገርና በድርጅት ፍቅር ያቆራኘንና በውስጡም ደብቆ ያኖረን ጉዳይ ቢኖር ይኸው የሀገርና የትግል መንፈስ ነው።

አንዲት የበግ ግልገል በጨካኝ ተኩላዎች በለሊት ልትበላ ትችላለች። ነገር ግን የደሟ ፍንጣቂ  በሸለቆዎቹ አለቶች ላይ መረጨቱ ስለማይቀር፣ የእውነት ጎህ ሲቀድና የጸሐይ ንጋት ስፍራውን ሲከበው ወንጀሉ ይፋ መውጣቱ አይቀሬ ነው። በመሆኑም ፈጣሪ አሟልቶና ቀድሶ በሠራት በዚች የመሪ ድህ በሆነች ሀገራችን፣ የአመጻኞች እግር፣ ደካሞችን የሚጨፈልቅበት፣ የጥፋት ምድር ከሆነች ዓመታት ተቆጥረዋል።  ከዚህ የመከራ ሰቆቃ ለማምለጥ ያ ትውልድ! የከፈለው መስዋእትነት ይህ ነው ብሎ በቃላት ለመግለጽ ያስቸግራል።

ለቁጥር የሚታክተው ወጣት በየአደባባዩና በየቅጥሩ ጀረባ ደረቱን በጥይት አረር እየተበሳ በጽናት አናቸንፋለን! ሞት ለፋሽስቶችና ባንዶች፣ ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ እያለ ሲዎድቅ፣ ገሚሱ በየግንቡ ውስጥ የፊጥኝ ተጠፍንጎ ረዥሙን የመከራና የሰቆቃ ዓመታት በቁሙ ሲጨልጥ፣ ሌላው በስደት የውርደትና የምጻተኝነት ህይወት እንዲገፋ ሲገደድ፣ ቀሪው ደግሞ የህሊና እስረኛ ሆኖ የኑሮን ጭላጭ እየተጋተ በሰቀቀን ኖሯል።

በትግል ዓለም የመታገያ መንገዶች ባይኖሩና ሁኔታዎች አመች ባይሆኑ፣ ዓላማን በጽናት ጠብቆ በትእግስት መቆየት በራሱ እንደ በረዶ ጠጥሮ በጊዜ ሂደት የራሱ ቅርጽ ይዞ ለመገለጥ ያስችለዋል። አሁን በኢ.ሕ.አ.ፓ መንደር እያየነው ያለው ጅምር ይህንኑ እውነታ የሚያስገነዝበን ነው። ሀገራችን የአባቶችንና የእናቶችን ትኩስ እንባ እስኪበቃት ጠጥታለች። በልጆቿም ንጹህ ደም አፈሯን አጨቅይታለች። ከእቅፏ ህያው ግልገሎቿ ተነጥቀው በድን አካላቸውን ታቀፋ እንድትቀር ተደርጋለች። ዛሬም ቢሆን ይኸው መቅሰፍት እጅና እግር አውጥቶ በአደባባይ ከሽንጎ ሲውል ታዬ እንጅ፣ ሊያስቆመው የቻለ አንዳችም ሃይል ከቶ አልተገኘም። እንደውም የትግሉን ውስብስብነትና መራራነት የበለጠ እያባባሰው ሔደ እንጅ።

በኢትዮጵያ የፍትህና የጭቆና ተጋድሎ ኢ.ሕ.አ.ፓ የማይነጥፍ ታሪክ አስመዝግቧል። በህይወት ደም እንዲለመልሙ የዘራቸው አበቦች ጨካኞችና አረመኔ መሪዎች እንዴት ነቅለው እነደጣሉአቸው፣ በደረት አቅፎ ያሳደጋቸው ግልገሎች እንዴት በአምባገንን ተኩላዎች እንደተበሉ አስተውሉ። የዜጎች የፍትህ ጥማትና ተስፋ፣ እንዲሁም የግፍ እርምጃና መዘዙ ካደረሱት ጥፋት ጉያ የመነጩ ትኩስ የምሬት እንባዎች በዜጎች ልቦና ውስጥ ደረቀው ቀርተዋል። ቀስት ወርዋሪ የሚያስወነጭፈውን ቀስት እንጅ ለማስፈንጠሪያ ያጎበጠው ደጋን እንደማያሳስበው ሁሉ፣ ነጻነት የምትወደው ድልን ራሱን እንጅ፣ በትግሉ መሰዋእት የሚከፍሉላት የቁርጥ ቀን ልጆቿ ህይወት አይደለም።

ንስር ማእበል ሲመጣ ከዳመና በላይ እነደሚውል ሁሉ፣ እንዲሁ ኢ.ሕ.አ.ፓም ታሪኩንና የትግል ወኔው ጠብቆ፣ በየጊዜያቱ ያጋጠሙትን ውጣ ውረዶች በጽናት በመወጣት እዚህ እንደደረሰ ይታወቃል። ወቅቱ የትግል ማእበል የሚነፍስበት እንደመሆኑ መጠን ቀሪውን ትግል በቀጣይ ለመስኬድ ይቻል ዘንድ፣ ከሀገር ወዳድና የአንድነት ሃይሎች ጋር በትግሉ ጎራ ግምባር ቀደም ሆኖ ለመሰለፍ ቆርጦ ተነስቷል። ስለሆነም የትግል አንድነት ጥሪ ማድረግ ከጀመረ እነሆ ሰንበትበት ብሏል።

ዛሬ ይህ የትግል ጥሪ በሀገር ወዳድ ወጣቶች ዘንድ አወንታዊ ምላሽ እያገኘ መምጣቱ የሚታወቅ ነው። ሰሞኑን የኢሕአፓ ወጣቶች ሊግ አሜሪካ ውስጥ ሁለተኛ ዓመት የምስረታ በዓሉን በአከበረበት ወቀት የነበረውን ሁኔታ የሚያሰይ ፕሮግራም በፓልቶክ የወይይት መድረክ በተላለፈበት ወቅት፣ ግለታቸው እንደመብረቅ የሚወረወር፣ ትነፋሻቸው የጠላት ጣር፣ ወኔአቸው የአንበሳ ደቦል፣ የሆኑ ብርቅዬ፣ በዓይንም በመንፈስም ሚዛን የሚደፉ ወጣቶች፣ በትግሉ ጎራ ብቅ ማለታቸውን ለመረዳት ችያለሁ። ስለሆነም ኢሕአፓ ልጆቿን እነደካባ ለብሷቸው እንደኖረና አዳዲስ ልጆችም በመንፈስ ጸንሳ በሆዷ ታቅፋ ስታምጥ እንደኖረች ደግ እናት፣ እነሆ ይኸው ዛሬ ተሳክቶለት ዓይኑን በዓይኑ ለማየት የበቃ አንጋፋ ድርጅት ሆኗል ማለት ይቻላል።

በሀገራችን ባህል አዲስ ልጅ ሲወለድ፣ አራስ ጥሪ ተይዞ ይጠየቃል። በክርስትና፣ በልደትም እንዲሁ ነው ባህሉ። ስንቶቻችን ይህን እንዳደረግን አላውቅም። ለኔ ይህ የሁላችንም የትግል ወኔ ሽል ውልደትና የድል ብስራቱ ትንሳኤ መባቻ ሆኖ ይሰማኛል። ይህ ደግሞ የህይወታችን ዋነኛ ዓላማና ጥልቅ ሚስጥር ነው። እንኳን ደስ አለን!! እንኳን ደስ አላችሁ!!!

ቀደም ሲል የትግሉ ዘር በማንኛውም መሬት ላይ ተዘርቶ ነበር፣ የምርት መሰብሰቢያው ቀን እጅግ ከመርዘሙ የተነሳ እልህ አስጨራሽና ተስፋ አስቆራጭ ሆኖብን ቆይቷል። አሁን ግን ፋኖሳችንን ከፍ አድርገን በውሰጡ የኢ.ሕ.አ.ፓን የትግል ዘይት ሞልተን የራሳችንን ነበልባል አብረተን የምናሳይበት ወቅት ላይ ደርሰናል። የዘራነውንም ምርት የምንሰበስብበትና ለቀጣይ ትግል ያልተበረዘ ዘር የምንለቅምበት ጊዜ ቢኖር ከመቼውም ጊዜ በላይ ወቅቱ አሁን ነው።

እናንት የኢ.ሕ.አ.ፓ- ወጣት - ክንፍ (ሊግ) አባላት፣ በሁላችንም ህሊና ለዘመናት በመንፈስ ተጸንሳችሁ በምኞት የተወለዳችሁ ልጆቻችን እንጅ እንግዶቻችን ባለመሆናችችሁ ደስታችን ወሰን የለውም። ወጣቶች በመሆናችሁ ህልማችንን የበለጠ ያለመልመዋል። ለትላንት ተጋድሏችን ብድራት ይሆን ዘንድ፣ በናንተ ውስጥ ነገን እንድናይ አድርጎናል። በዜግነት አይኖቻችን የፊታችሁን ገጽታ ለማየት አይኖቻችን ሲናፍቁ ኖረዋል። ከእንግዲህ የትግሉ ማእበል አይለያየንም። ጥላችሁ በፊታችን እነደሚያበራ ማሾ ነው። በብቸኝነት ዘመናችን የልባችንን ትርታ አዳምጣችሁዋል። በነቃችሁ ጊዚም ልቅሷችንን በአይናችሁ አስተውላችሁዋል። እነሆ ዛሬ ደግሞ ደስታችንን እንለግስላችኋለን። የዛሬው ደስታችን የትላንቱ መራራ ትግል ትሩፋት ነውና። እኛ የምንወዳችሁን ያህል አስፋላጊውን የሞራልና የፍቅር ዘውድ ልንጭንላችሁ ዝግጁ ነን፡፤ በአንጻሩ ደግሞ የምናሳድጋችሁን ያህል በተመክሮአችን ልንከረክማችሁ እንደምንወድ እንድታውቁልን እንፈልጋለን።

ጭቆና እንደአውሎ ንፋስ ይጋረፋል። የጭቆናን ቀንበር መስበር ደግሞ በጽናት መታገልና መሰዋእትነት መክፈልን ይጠይቃል። “ለመታገል ድፈር፣ ለማሸነፍ ቁረጥ” የሚለው ቀደምት አባባል ዛሬም ቢሆን ይሰራል። በሀገራችን ሕይወት በነጻነት እጇን ዘርግታ ስታውለበልብ ማየት የምትናፍቁ ወጣቶች ሁሉ፣ ልንመክራችሁ የሚገባን ነገገር ቢኖር፣ የማይናወጥ ተነሳሽነት ከሌለ ትግላችሁን አረም ይወርሰዋል። እውቀትና ልምድ ካልታከለበት ተነሳሽነት ብቻውን መደናበር ይሆናል። ሁሉም ነገር በተግባር ካልተመራ ፋይዳ ቢስ ነው። በዚህ ሁሉ የመንፈስና የዓላማ አንድነት፣ እንዲሁም የአሰራር ቅንጅት ከሌለ ከንቱ ውዳሴ የማነብነብ ያህል ነው።

የምንነግራችሁ ቁም ነገር እንጅ ሌሎች እንደሚያነበንቡት ከአይምሮ ድግስ የተቃረመ ፍርፋሪ አይደለም። በትግሉ ጉራ አባራሪ እንጅ ተባራሪ ሆናችሁ ማየት አንፈልግም። የቀናተኛ ዝምታ በጩኸት የተሞላ ነውና በአንዳች ድመጽ አንዳትናወጡ ከወዲሁ ልንመክራችሁ እንወዳለን። ደግሞም በእጃችሁ ያለውን ነገር ከእኛ መጠበቅ የለባችሁም። ኢ-ሰብአዊነት ከሀገራችን እስኪጠፋ ድረስ የትግል ፋና ይዘን መሮጥ ይጠበቅብናልና።

ብዙዎች ነጻነታቸውን እነደ እጅ ካቴና ታስረውበት ይዞራሉ። እናንተ ግን በማስተዋል ንጋት የታሰራችሁበትን ሰንሰለት በጥሳችሁ ከፍ ብላችሁ የሀገርና የወገን አርነት ለማስከበር በቆራጥነት ዋርድያ በመቆማችሁ ልባችን በእጅጉ ሀሴት ያደርጋል። ትግላችን እመርታን ያሳየበትና፣ ወደ ሌላ ምእራፍ መሸጋገሩን በይፋ ያረጋገጥንበት ነው። ኩራታችንም የሚመነጨው ከግብዝነት ሳይሆን ህያው ሆኖ ከተቀዳው ከዚህ ሀቅ በመነሳት ነው።

በሀገር መውደድ ፍቅር አንዴ ተቆራኝተናል፣ ከእንግዲህ አንዳች የሚለያየን የለም። አጥብቀን ወደናችሁማል። ድምጻችንን ከፍ አድርጎ ወደ እናንተ እንጮሀለን፣ በትግሉም ዘርፍ ከፊት ለፊታችሁ መቆም እንመኛለን። ትግሉ ወደሁዋላ ስለማይመለስ፣ ጊዜው ከሚጠይቀው የትግል ስልትና ስነምግባር ጋር ፈጥኖ መዋሀድ ያስፈልጋል። በተቀናጀ መንፈስና በጠነከረ የትግል ክንድ ትግሉን ወደፊት ማስኬድም ይጠበቅብናል። በዚህ ረገድ የተጫነባችሁ ሀገራዊ አደራና በጫንቃችሁ ላይ የወደቀው ሀላፊነት ታላቅ እንደሆነ አበክረን እናውቃለን። ትኩረታችሁ ውጤቱ ላይ እንዲሆን እንጂ፣ በትግሉ ሂደት ውስጥ በሚከሰቱ ውስብስብና አስቸጋሪ ክስተቶች፣ በአንዳችስ እንኳ ልባችሁ እንዳይወድቅ፣ አደራችን የጠበቀ ነው።

ከእንግዲህ ፍቅራችን አያስፈራችሁም፣ ፍላጎቶቻችንም አይገድቧችሁም። ከጠላቶቻችን ጋር እኩል የምንሆነው ስንሞት ብቻ ነውና፣ አይዟችሁ! በርቱ! እሰየው! እደጉ! ተመንደጉ! እንላለን።

ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!
ኢ.ሕ.አ.ፓ ያቸንፋል!
እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ!!

Ahailu99@gmail.com

አክሊሉ ሃይሉ
ከፍራንክፈርት
(ኦክቶበር -2011)